# ገዢው ወያኔ ነው ፤ ወያኔም ትግሬ ነው !

ምናልባት በቅርቡ ሕግና ስርአት ተለውጧል መሰለኝ ፤ ቀድሞ የማውቀውንም ሰው እንኳን በሥሙ ለመጥራት እያስፈራኝ መጥቷል ። እድሜ ዘልዛላው በስተመጨረሻው ላይ ምኑን ያሰማኝ ጀመር? አዬ ጊዜ! የፈሪዎችና ያድር ባዮች ዘመን ላይ ይጣለኝ? ያሳዝናል ፤ ቢከፋም ቢለማም ሀሰትን ተገን አድርጎ ከመጠለል ይልቅ ፤ እውነትን ተገን አድርጎ መጠለሉ ማንን ገደለ? ልብ የሚያምነውን አፍ ሲክደው መመልከቱ ! ግሩም ነው ፤ አንድ ሰው በገዛ አይምሮው ውስጥ ሁለት የማይጣጣሙ ተፃራሪ ነገሮችን ይዞ ሲኳዝና ሲያስተናግዳቸው መመልከቱ አጁብ ድንቅ የሚያሰኝ ነው ።

በቅርቡ አንድ የውይይት መድረክ ውስጥ ገብቼ ሳደምጥ ሥምን በተመለከተ ጉዳይ ትልቅ ውዝግብ ውስጥ ገብተው በማስተዋሌ ነገሩን እስኪቋጩ ካድምጥ ብዬ ረዘም ላለ ሰዓት ተቀምጬ ሳደምጥ ቆየሁ ፤ ሆኖም ግን ያወዛገባቸው ርዕስ ሳይቋጭ ካለመስማማት የተስማሙ ይመስል ሁሉም እንደየ እምነታቸው እንደሚቀጥሉበት በማስረገጥ የጋራ የሆነ አቋም ላይ ሳይደረስ መድረኩ ተዘጋ እኔም ወደጉዳዬ ሄድኩ ።

የርዕሱ አነጋጋሪ ዋና ምክንያት የነበረው አሁን ኢትዮጵያን እያመሰ ያለው የወያኔ አገዛዝ "የትግሬ" መንግሥት" ነው ብሎ መጥራቱንና አለመጥራቱን በተመለከተ ነበር ።

እኔም በመድረኩ ላይ ባድማጭነት እንጂ በተሳታፊነት አልታደምኩም ነበርና ፤ ይሄው እኔም እምነቴና አቋሜ ይታወቅልኝ ዘንድ ይህንን ጽሑፍ ለማቅረብ ተገድጃለሁ ።

በመሰረቱ ይህ የውይይት መድረክ ለምን ይህን ርዕስ እንደመረጠና እንዴትስ ሊያወዛግባቸው እንደቻለ ባይገባኝም በኔ እምነት ግን ዛሬ ኢትዮጵያን እየገዛና አፈር ድሜ እያስጋጠ ያለው "የትግሬ መንግሥት" ነው ። ስለሆነም ትላንትም ፤ ዛሬም ሆነ ነገ ፤ ይህ  አገዛዝ ከኢትዮጵያ ጫንቃ ላይ እስካልተወገደ ድረስ ሁሌም የምጠራው "የትግሬ መንግሥት" ብዬ ነው ።

<u>በቀላል አማርኛ ወያኔ ትግሬ ነው ፤ ትግሬም ኢትዮጵያን እየመዘበረና እየገዛ ነው ፤ ትግሬ ግን ወያኔ አይደለም ፤ (ሕዝቡ ወያኔ ሳይሆን ከሕዝቡ የተወለዱትና የወጡት ዛሬ አገራችንን እያመሷት ያሉት ግን ወያኔውች ናቸው) እውነታው ይህ ነው</u> ። ይህ አገላለጽ ያልገባው ካለ አዝናለሁ ፤ ከዚህ በተሻለ ቋንቋ መግለጽ አልችልምና መቼስ ማልጎደኒ ፤ ያቅሜን ሞክሪያለሁ ።

እዚህ ላይ ግን አንድ ነገር ካስገነዝብ እወዳለሁ "የትግሬ መንግሥት" ብዬ ስጠራው ጥሪዬና ስያሜዬ ገዢውን እንጂ ሕዝቡን እንዳልሆነ ካሰምርበት እወዳለሁ ። <u>የትግሬ ሕዝብ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ  ወገኖቼ  ከአብራኩ በወጡ ልጆቹ እየተገዛ ሳለ በሥሙ ይነገዳል ። አራትና አምስት ሚሊዮን የሚሆነው የትግሬ ሕዝብ  መንግሥት ሊሆን አይችልምም ፤ አይደልምምና ።</u>

ሌላው የሚያምታታው ነገር ቢኖር "የትግሬ መንግሥት" ብዬ የምጠራውንና "የትግሬ ሕዝብ የሥርአቱ ተጠቃሚ ነው" የሚለው ጉዳይ ስለሆነ ፤ እዚህ ላይ የማቀርበው ስለ ትግሬ መንግስት እንጂ ፤ የትግሬ ሕዝብ ከስርአቱ ስላገኘው ጥቅም አይደለምና በቅድሚያ የተነሳሁበትን ርዕሴን አጢኑልኝ ። የትግሬ ሕዝብ በስርአቱ ተጠቃሚ ነው ፤ አይደለም ፤ የሚለው ጉዳይ እራሱን የቻለና በራሱ ሰፊ ትንታኔ ሊሰጠው የሚገባ ስለሆነ ከተነሳሁበት አርእስት ጋር እንዳታምታቱብኝ በቅድሚያ አሳስባለሁ ።

በመሰረቱ ያለፉትን ኢትዮጵያን ያስተዳደሩ መንግሥታዊ ስርአቶችን ብንቃኝ ፤ ብዙ ጊዜ የሚነሱትና የሚጠቀሱት ከአፄ ምኒሊክ እስከ ደርግ ዘመነ መንግሥት ያሉት አስተዳደሮች ናቸው ። ዛሬ እንደምሰማው ባንዳንድ ደካሞች የተዛባ አጠራር "የአማራው መንግሥት" እየተባሉ የሚጠሩት

ማለት ነው ፤ ይህ ስያሜ በአብዛኛው ኢትዮጵያዊ እይታ ተቀባይነት ባይኖረውም ፤ ነገር ግን ከኢትዮጵያ አገራችን መልካም ምኞት በሌላቸው እንደ ኦነግ ፤ ኦብነግና ወያኔ ፤ ወይም ዛሬ በስልጣን ላይ ያለው "የትግሬው መንግሥትን" የመሳሰሉት የሚያራግቡት የተንሸዋረረ አመለካከትና ተራ ፍሬ ፈርስኪ ፕሮፓጋንዳ ነው ።

መጀመሪያ እኔ "የትግሬ መንግሥት" እያልኩ ወደምጠራው ትንተና ከመሄዴ በፊት በዚህ "የትግሬ መንግሥትና" በቀደሙ ኢትዮጵያን ባስተዳደሩ ነገር ግን በጸረ ኢትዮጵያ ቡድኖች የአማራው መንግሥት እየተባሉ ስለሚጠሩት በሁለቱ በኩል ያለውን ትልቅ ልዩነት በተቻለ ለማስረዳት እሞክራለሁ ።

እስቲ ግን ወደዚያ ከመሄዴ በፊት ይህንን ጽሁፍ በመጫን የወያኔ ቁንጮ የሆነው ስብሃት ነጋ በመባል የሚታወቀው ግለሰብ ከዝጉብኝ እንደወጣ ባልተሟሸ አፉ የሚለውን ያድምጡ

ይህ የአማራው መንግሥት እየተባለ በብተና ካህኖች የሚጠራው የአፄ ምኒሊክ ፤ የአፄ ኃይለሥላሴም ሆነ የደርግ ስርዓተ መንግሥት ዛሬ አለሃፍረትና ይሉኝታ በትግሬ ተወላጆች ብቻ ከላይ እስከ እታች እንደተወረረው የስልጣን ተዋረድ በአማራው የተያዘ አልነበረም ። በቀድሞው መንግሥታዊ ስርአት በቁኝጮነትም የተቀመጡ መሪዎች ቢሆኑም የዘር ሀረጋቸው ቢጎተት ከአማራነት ይልቅ ወደ ሌላ ጎሳ የሚያደሉ እንደሆነ ይታወቃል ። ሆኖም ግን ወደነሱ የዘር ሀረግ ጉተታ አልገባም ፤ ስለነሱ የዘር ሀረግ ብዙ የተባለና የተፃፈ ስለሆነ ፤ ፍላጎቱ ያለው አስፈላጊውን ምርምር አድርጎ ሊደርስበት ይችላልና የተነሳሁበትን ቁም ነገሬን እንዳያስተኝ ምርምሩን ላንባቢያን እተወዋለሁ ።

ከላይ በዘረዘርኳቸው ሶሥት መንግሥታዊ ስርአት መዋቅር ውስጥ በአስተዳደርና በመሪነት ተቀምጠው የነበሩ ግለሰቦች ዛሬ በታኞች እንደሚዘባርቁት ከአማራው ብሄር የተውጣጡ ሳይሆኑ ፤ እውነቱ ፤ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ያቀፈና እንዲያውም ዛሬ ካለው አገዛዝ ጋር ሲነፃፀር እንደምሳሌነትና እንደ አብነት ሊጠቀሱ የሚገባቸው ሁሉን አቀፍ መንግሥታዊ አስተዳደሮች እንደነበሩ ነው ።

መነገር ካስፈለገ ባለፉት ሶሥት ስርአቶች ባብዛኛው መንግሥታዊ መዋቅር በበላይነት የስልጣን ኮራቻውን ይዘው የነበሩት በአንደኛ ደረጃ ኦሮሞ ፤ በሁለተኛ ደረጃ ትግሬ ፤ በሶሥተኛ ደረጃ አማራ እንደሆነና እንዲያም እያለ በሐገራችን ያሉትን ጎሳዎች ሁሉ ያካተተ እንጂ ዛሬ እንደሚደሰኩረው ተረት ፤ ተረት ፤ እንዳልነበረ ከማንም የተሰወረ አይደለም ።

<u>ለተጨማሪ መረጃ "ኢትዮጵያን ማን ገዛ" የሚለውን ከአፄ ምኒሊክ እስከ ደርግ ዘመነ መንግሥት የነበሩትን ከፍተኛ የባለስልጣናት ሥም ዝርዝር ለመመልከት እዚህ ላይ በመጫንም ሆነ አንዳንድ ድረ ገፆችን በመጎብኘት መመልከት ይቻላል</u>

ከዚህ ሁሉ መሰረተ ቢስ ውዥንብር መንስኤው የአማርኛ ቋንቋ የአገራችን ብሄራዊ ቋንቋ መሆኑ እንደሆነ ከማንም የተሰወረ አይደለም ። ከዚያም በመነጨ የብተና አቀንቃኞች ስውር አላማቸውን ለማሳካት ሲሉ የአማርኛ ቋንቋን ማደግ እነሱ እንዲታመንላቸው ከሚጥሩትና ከሚደክሙበት የአማራው አገዛዝ ብለው ከለጠፉት መሰረተ ቢስ ውንጀላ ጋር ሊያጎዳኙትና የተወላገደ ታሪክ ለመመዝገብ ፤ ህልማቸውንና ምኞታቸውን ዕውን ለማድረግ ፤ እንደ ዋና መሳሪያ አድርገው ለመጠቀም ላይ ታች የሚዋትቱበት አላማ እንጂ ፤ ምንም እውነታን ያልተላበሰ የደካሞች አሉባልታ እንደሆነ ይታወቃል ።

የአማርኛ ቋንቋም የብሄራዊ ቋንቋ ሊሆን የበቃበትና ቋንቋውም እያደገ መምጣት ፤ ብሎም በአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ተቀባይነት ማግኘት ፤ እራሱን የቻለ አንድ ሰፊ ትንታኔ የሚፈልግ ስለሆነ ወደሱ ሳልገባ የቋንቋው ማደግ ግን አፍራሾች እንደሚሉት የአማራ መንግሥት ስልጣኑን በመያዙና

ያ... የአማራ መንግሥት ብለው የሚጠሩት በሌሎች ቋንቋዎች ላይ ባደረገው ተጽዕኖ ወይም ጭቆና የወጣና እራሱን ያዳበረ እንዳልሆነ ግን ሳላስገነዝብ አላልፍም ።

ወደተነሳሁበት ርዕስ ስመለስ አውቀንም ይሁን ሳናውቅ ወይንም ሆን ብለን ነገሮችን ለማንሻፈፍ ካለን ጽኑ ፍላጎት ካልሆነ በቀር ዛሬ ኢትዮጵያን አፈር ድሜ እያስጋጠና እየገዛ ያለው "የትግሬ መንግሥት፤ ነው ። እደግመዋለሁ "የትግሬ መንግሥት" ነው ።

ለምን የትግሬ መንግሥት እንዳልኩት በተቻለ ለመዘርዘር እሞክራለሁ ። በመጀመሪያ ከላይ <u>በቁኝጮነት የተቀመጠው ጠ/ሚኒስትሩና ጠቅላላ የፖሊት ቢሮ አባላት በሙሉ የትግሬ ተወላጆች ናቸው ። የህወሃት (ወያኔ) አባሎች ናቸው ። ባብዛኛው መንግሥታዊ መዋቅር ውስጥ በበላይ አዛዥነት ከፍተኛውን መንግሥታዊ ስልጣን የያዙት በሙሉ የትግሬ ተወላጆች ናቸው</u> ። ከብዙ በጥቂቱ ፤ በጸጥታ ፣ በፍርድ ሚንስትር ፤ በአምባሳደርነት ፤ በፖሊስና በመከላከያ ሰራዊቱ ከፍተኛ ቦታዎች በሙሉ ወይንም ባብዛኛው የትግሬ ተወላጆች ናቸው ።

አንድን መንግሥት ከአንድ ጎሳ የተውጣጣ ነው ብሎ ለመናገር በመጀመሪያ መመልከት የሚኖርብን ያንን መንግሥት ሳይንገዳገድ ጸንቶ እንዲቆም የሚያደርጉትን መንግሥታዊ መዋቅሮች ውስጥ በከፊተኛ ባለስልጣንነት ያስቀመጣቸውን ግለሰቦች መመልከቱ ለጥያቄው አጥጋቢ መልስ ይሰጣል ብዬ አምናለሁ።

እንግዲህ አግዜር ያሳያችሁ የትግሬ ሕዝብ ከጠቅላላው ኢትዮጵያ የሕዝብ ብዛት ሲነፃጸር ከአራት ወይም ከአምስት በመቶ አይበልጥም ፤ ነገር ግን አገሪቱ ካላት ከፍተኛ መንግሥታዊ መዋቅር ውስጥ ሰማንያ በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የሚሆነውን ይዘው ይገኛሉ ።

በተለይ የጸጥታ ፤ የፖሊስና የመከላከያ ሰራዊቱ ከሃምሳ አለቃ እስከ ጀኔራል ያለው የማዕረግ እርከን ንፋስ በማያስገባ ሁኔታ ጥቅጥቅ ተደርጎ የታጠረው በትግሬ መኮንኖች ነው ፤ ይህ እንደሌላው የሲቪል ባለስልጣናት ሰማንያ በመቶ የተያዘ ሳይሆን ፤ መቶ በመቶ የተያዘ እንደሆነ ይታወቃል ። ይህ ሁሉ አድሎዋዊና ጎጠኛነት በነገሰበት በወያኔ ስርአት ፤ አንድን መንግሥት እንደ መንግሥትነት ሊቀጥል የሚያስችሉትን ከፍተኛ የሆኑ የስልጣን እርከኖች በሙሉ በአንድ ጎሳ ተወጥሮና ታጥሮ እያየሁ ታዲያ ምን  ብዬ ልጥራው ? "የትግሬ መንግሥት" ማለት አግባብነት ከሌለው ፤ ታዲያ ! የሴራሊዮን መንግሥት ልበለው? ተዉ እንጂ! እየተስተዋለ ።

ለመሆኑ ባለፉት  ሶሥት ስርአቶች ውስጥ በየትኛው ስርአት ውስጥ ነው ከአማራ ብቻ የተውጣጣ የጦር ሰራዊት የተቋቋመው? ዛሬ ግን በትግሬው አገዛዝ ውስጥ አጋዚ የሚባል ከትግሬ ጎሳ ብቻ የተውጣጣ በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሰራዊትን የገነባን ወያኔን ፤ ጎጠኛ መንግሥት አይደለም ብሎ መደስኮር እራስን ከማታለል ወይም ያለውን የጎጠኛ ስርአት ከመለማመጥና ከመፍራት ፤ አሊያም በራስ ካለመተማመን የመጣ በሽታ ካልሆነ በቀር  ሌላ ምክንያት ሊኖረው አይችልም።

ይህ አይነት አይን ያወጣና ጥርስ ያገጠጠ የጎጣኛ ስርአት በአፄ ምኒሊክ ዘመነ መንግሥትም ሆነ ከዚያ ስርአት በኋላ በመጡት መንግሥታዊ ስርአቶች አልታየም ። እንዲህ አይነት ጨፍኑና እናሞኛችሁ አይነት ወንጀል ተደርጎም አያውቅ ፤ ዛሬ ግን የምዬን ላብዬ የሆኑ ዘመነኞች ወተት ጥቁር ነው ፤ ውሃ በመጥረቢያ ይፈለጣል ፤ የአለት ንቃት በወስፌ ይጠገናል፤ ሲሉን አዎ ልክ ነው እያሉ  ማራገብ ፤ ያስተዛዝባል ፤ በዚህ ሁኔታ አድር ባዩ ፤ ፈሪው ፤ ካድሬው ባንድ ላይ ተሰልፎ እንደ አሚና በየ ሰዉ ደጃፍ እየዞሩ ሲለፈልፉ ቁጭ ብሎ መመልከትና እውነቱን አለማስተማር ኢትዮጵያዊነት አይደለም ።

የሚገርመው ግን ማንም ጎጠኛ እየተነሳ ያለፉትን መንግሥታት ሁሉ የአማራው  መንግሥታት ፤ ነፍጠኞች ፤ እያለ ሲያላዝን ፤ በሌላው ወገን ደግሞ ዛሬ አይናችን እያየ እጃችን እየዳሰሰ ያለውን

“የትግሬን መንግሥት” ለምን የትግሬ መንግሥት አላችሁ ብሎ ቡራ ከረዩውን ስሰማ የዚህ ሁሉ ማደናቆር መንስኤው ምን ይሆን ብሎ መጠየቁ አግባብነት አለው ብዬ አምናለሁ ።

በመሰረቱ ባለፉት ሶሥት መንግሥታዊ ስርአቶች አንድን ጎሳ በመንግሥት ደረጃ የሰደበ ፤ ያንቋሸሸ ፤ ያሳደደ የለም ። ዛሬ ግን “የትግሬው መንግሥት” በአማራው ላይ ሕዝብ እንዲነሳሳ ያደረገ ፤ የአማራውን ሕዝብ ያስጨፈጨፈ ፤ በአደባባአይ ወጥቶ የአማራ ነፍጠኞች በማለት ሊያናንቅ የሞከረ ፤ መሆኑ እየታወቀ ዛሬ እኛ የትግሬ መንግሥት አትበሉ የምንባልበት ምክንያቱ ሊገባኝ አልቻለም ።

የትግሬ መንግሥት አይደለም ብሎም ያሳመነኝም የለም ፤ ሊያሳምነኝም አይችልም ፤ እንደ ማስተዛዘኛ የሚጠቀሙት ከአማራውም ሆነ ከኦሮሞ ወይንም ከሌላ ጎሳ የመጣ ወያኔ እንዳለ ነው ። እነኚህ በገብስ ቆሎ ላይ እንደ ኑግ የተበተኑ ወያኔዎች አንደኛ ትግሬዎች አይደሉም ፤ ወያኔ ለመሆን ትግሬ መሆንን ይጠይቃል ፤ ከስሙም እንደምንረዳውና እንደነሱም አላማ “ሕወሀት” “የትግሬ ነፃ አውጪ” እንጂ የአማራ ወይም የኦሮሞ ነፃ አውጪ ማለት አይደለም ። ስለሆነም እንዲያው ለለጋሽ አገሮች ሕብረ ብሄር ለማስመሰል የተቀላቀሉ መለመኛ ጉዶች እንጂ ፤ ወያኔ በደደቢቱ የወያኔ ሂሳብ የሚመለከታቸው ሳይሆኑ (Naturalized ) ወያኔዎች አድርጎ ነው የሚመለከታቸው ፤  ስለሆነም ልክ እኛ በያለንበት አገር የወሰድነውን ዜግነት ጥፋት አጠፋችሁ ተብለን ዜግነታችንን እንደምንገፈፍ ሁሉ እነዚህም ከሌላ ጎሳ የተውጣጡ ወያኔዎች አሸዋ ክምር ላይ የቆሙ ወያኔዎች በመሆናቸው ወያኔነታቸውን ባማናቸውም ጊዜ ሊገፈፉ የሚችሉ ሁለተኛ ደረጃ ወያኔዎች ናቸው ። ስለሆነም የነዚህ ወዶ ገባ ወያኔዎች በመሃከላቸው መኀለት የትግሬ መንግሥት አይደለም ካለማለት አጥጋቢ መከራከሪያ አይሆንም ።

ሌላው አስገራሚ ነገር ቢኖር ባብዛኛው ሰዉ አማራ ፤ ኦሮሞ ወዘተ…ብሎ ለመጥራት ምንም ችግር የለበትም ፤ ነገር ግን “ትግሬ” ብሎ ለመጥራት ግን እንደ ሃጢያት ይሁን ፤ እንደ ወንጀል ፤ የሚታየው አልገባኝም ፤ ምናልባት ቃሉ ላይ እኔ ያልተገነዘብኩት አስፈሪ የሆነ ነገር እንዳለ ለመረዳት ብዬ “ትግሬ” የሚለውን ሆሄያት ማጤን ጀመርኩ ። ያደረኩትን ባደርግ ያው እንደሌላው  የአማርኛ ሆሄያት ከመሆን በቀር ፤  ምንም እንከን አላገኘሁባቸውምና የሕብረተሰቡ ፍራቻ ከምን የመነጨ እንደሆነ እንቆቅልሽ እንደሆነብኝ አለሁ ።

እንግዲህ አንድ ሰው ወላጆቹ ባወጡለት ሥም ይጠራል ፤ ወላጆቹ ካወጡለት ሥም ውጪ በጎረቤት ወይም ባካባቢው ህብረተሰብ በሌላ ሥም የሚጠራ ከሆነ ያ ትክክለኛ ሥሙ ሳይሆን “ቅጽል” ሥም በመባል ይታወቃል ፤ ታዲያ አማራውን ፤ አማራ ብለን ስነጠራ ፤ ኦሮሞውን ፤ ኦሮሞ ብለን ስንጠራ ፤ ጉራጌውን ፤ ጉራጌ ፤ ብለን ስንጠራ ፤ ለምን ትግሬ ጋ ስንደርስ ፤ ትግሬ አትበሉ እንባላለን? ታዲያ ማን ብለን እንጥራቸው? ሥማቸው ተቀይሮስ ከሆነ ለምን ይፋ አይሆንምና ባዲሱ ስማቸው አንጠራቸውም ? ይህ ሳይሚካ እንዲያው በደፈናው ትግሬ አትበሉ የሚባልበት ጉዳይ ሚስጥሩ ስላልገባኝ ፤ የገባው ካለ ቢያስረዳኝ እወዳለሁ ።

ይህ ብቻም አይደለም ፤  ወያኔም አትበሉም ይባላል ፤ እንዴት ለራሳቸው ያወጡትን ሥም ሌላው ሲጠራው ጸያፍ አባባል እንደሆነ ሊያስረዱ ሲሞክሩ ይገርመኛል ። እነሱ በስማችን አፈርን ሳይሉ እስከ ዛሬ ድረስ የወያኔ 30ኛ  ፤ 30 ምናምነኛ ዓመት አከበርን እያሉ ሲቦተልኩ ነውር ነው ወያኔዎች ነን አትበሉ  አይባልም ፤ በነሱ አፍ ሲጠራ ይቀበሉታል በሌላው ሲሆን ወንጀል ይሆናል ፤ ዘመነ ግርምቢጥ ማለት እንግዲህ ይሄ ነው ።

ወደ ግራም ወደ ቀኝም ብናገላብጠው ፤ ወያኔ ትግሬ ነው ፤ ትግሬም ኢትዮጵያን እየገዛ ነው ፤ ስለሆነም ዛሬ አገራችን ኢትዮጵያን እየገዛ ያለው የትግሬ መንግሥት ነው ! ሃቁ ይሄው ነውና እንቀበለው ።

<u>ማሳሰቢያ</u>: -

እዚህ ላይ አንድ ማሳሰብ የምፈልገው ነገር ቢኖር የትግሬ ምሁራን (Elite) የኢትዮጵያን ሕዝብም ሆነ ኢትዮጵያን ከድተዋል ፣ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ አሁን ካለው አገዛዝ ጋር በመሰለፍ ኢትዮጵያን ለማዳን በሚደረገው ማናቸውም ጥሪ ተባባሪም ፣ ተሳታፊም ለመሆን ፣ ፈቃደኝነት ባለማሳየታቸው ፣ በነዚህ ምሁራን ላይ የሚሰነዘረውን ማንኛውንም አይነት ወቀሳም ይሁን ውግዘት ፣ በትግሬ ሕዝብ ላይ እንደተሰነዘረ አድርገው ለማቅረብ የሚፈልጉ አንዳንድ የዚሁ አገዛዝ አጫፋሪዎች ስላሉ የትግሉ አላማና እየተደረገ ያለው ትግል ከአገዛዙና አገዛዙን ከሚደግፉ ምሁራን ጋር እንጂ ከሕዝብ ጋር እንዳልሆነ ማስተማሩ ተገቢ ነው ። በመሰረቱ ምሁር ምንም እንኳን ከሕዝብ መሃከል የወጣ ቢሆንም ነገር ግን ምሁር ማለት ሕዝብ ማለት እንዳልሆነ መታወቅ አለበት ፣ ይህንን ከምሁሩ የተሰነዘረውን አባባል ከሕዝብ እንደተሰነዘረ አድርጎ ሕዝብን ከሕዝብ ለማለያየትና ለማቃቃር የሚደረገው ተራ ማደናገር ካገዛዙ አገልጋዮች እንደመጣ ተገንዝቦ ተቀባይነት እንዳይኖራቸው ሕግረተሰቡን በትጋት ማስተማር ተገቢ ነው ።

ድል ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ !

ከአይምሮ ዳኛቸው

# Who ruled Ethiopia? The myth of 'Amara domination'

**(The following document tries to demystify "Amhara domination" while supporting Dr. Tseggai Mebrahtu's educational article: “Modernisation: a poisoned chalice for Ethiopians” - Aug 6: ethiomedia)**

*** * * ***

**Are they fully aware of what they are advocating for when they accuse a single ethnic group, in this case Amara, of what they call “Amara national domination” and in particular “Shewan supremacism”?**

This is precisely analogous to the 1930-40’s European fascisms of victimisation by “race”, in this case victimisation by ethnicity to achieve the means and meat the ends of their own hidden agenda of expansion of “empires” at the cost of their neighbours. The exact analogy with European fascism is, Europeans by scapegoating a certain group/ethnicity/nations also justified their expansion of Empires at the cost of the neighbouring people/states territories and or overseas empires which reached its momentum immediately after 1492 (In what we can call post Christopher Columbus Europe).

Each of the groups: TPLF, EPLF/affiliated organisations and the OLF have had and still have their own agenda and reason.

In relation to Eritrean and pro Eritrean liberation movements and in particular the TPLF, Dr Tseggai Mebrahtu has given a detailed analysis and an educational article.

I can add one important point here concerning the TPLF. The TPLF leaders while engaged in scapegoating Amara's and disseminating lies, disinformation, defamation, biased and incorrect interpretation of history, on the other hand they see it just in all occasions to occupy and annex a huge (what they in public declared "a lions share") territory of Begemidir (Gonder) of Setit, Humera and so-called Falasha" land incorporating it to Tigray.

On the other hand the OLF and affiliated organisations, which was the ally of the TPLF till 1992, have also been and is still today engaged in the same act for a long time. To understand the real situation, however, one has to go back to the historical period of during/immediately before and after 1535 of Grang Muhammed's and his followers Jihad war for conquest. While accusing Amara's as settlers in "their" territory, what has happened is exactly the vice versa! It they who have been and continue to be engaged in expansion of empires at the cost of the scapegoated and victimised Amara's.

What concerns the "Amara domination" and or "Shewa Amara supremacism" I hereby present for everybody to see a list of leaders that have ruled Ethiopia from Emperor Minilik to the Derg.

## THE RULERS OF ETHIOPIA (WHO RULED ETHIOPIA IN THE PAST?)

1. Emperor Minilik - FatherHaile Melekot (Amara); Mother, W/o Ejigayehu (Oromo)

2. Emperor Hailesselassie - Father Mekkonen Woldemikael Gudesa (Oromo and Amara) and Ato Welde Melekot Yemane Kristos was only his parental father (Asadagi Abbat), who was a Tigrean noble from Tambien who had moved to Shewa, Mother W/o Yeshimebet (Gurage) Ali AbaJiffar (a daughter of an Oromo Chieftan of Wello) Woizero Yeshimebet died before her son was 2 years old. And his second wife was weizero Welete Giorgis Yimeru, (a Gurage) once married to Ras Darge Sahle Selassie (Minilik II's uncle), who is not Haileselassie's mother.

## Persons in political power during Emperor Minilik and Haileselassie's time:

## Oromo:

Ras Abbebe Aregay Bichire – Defence Minister
Bilata Deresa Amintu – Vice Minister of ministry of Agriculture
Dejazmach Deresu Duke – Governor general of Illubabur and Gemugofa
Dejazmach Fikreselassie Habtemariam – Governor General of Wellega
Dejazmach Kasa weldemariam – President of Addis Abeba University and Minister of Agriculture
Dejazmach Shiferaw Balcha – Administrator of Wellega and Abegaz of Jijjiga and Ogaden
Dejazmach Kifle Dadi – Governor of Gonde
Dejazmach Sebsibe Shiberru – Governor of Arussi
Dejazmach Bekele Weya – Adminstrator of Chebbo and Gurage and later on Adinistrotor of CherCher (Harer)
Dejazmach Kebede Bizuneh – Governor of Kibre Mengist (Adola), Nazareth (Yerer Kereiyu) and Menagesha
Fitawrari Hailemikael Zewde Goben-?
Fitawrari Lemma WeldeTsadik – Vice Governor of Sidamo
Lut. General Jagamma Kello – Commander of the forth army division and Governor of Bale
Maj. General Mulugeta Buli – Commandor of the Body Guard and Minister of Culture
Maj. General Abebe Gemeda – Commandor of the Second army division, Vice minister of Finance, Commandor of the Police and in charge of the Body Guard
Maj. General Wakjira Wereda – In charge of various army divisions
Maj. General Kelbesa Bekka – Administrator of Sidamo and Tigray
Maj. General Abera Weldemariam – Vice Commandor of the Air Force

Maj. General Regasa Jimma – Commandor of various army divisions
General Demise Bultu – Commandor of the second army division and Comandor of the Army
General Tadesse Birru –Comandor of the police and special forces
General Dawit Abdi – Comandor of the army's engineering division
Col. Solomon Kedir – Vice minister of customs and (yehizb dehninet minister)
Lutenant Girma weldegiorgis – Vice minister of the civil aviation and member of the Senet
Legaba Bekele Hordofa Chengire – Responsible of the Royal Palace (Gibbi)
Ato Yilma Deresa Amentu – Ethiopian Ambassador to the U.S.A, Minister of Foreign Affairs, Minister of Finance and Trade
Ato Gebremariam Amentu – Advisor of Telecomunications and Finance
Ato Amanuel Abrham – Ambassodr, Minister of Police and telecommunications, Advisor and member of the Crown Concil
Ato Bulcha Demeksa – Vice minister of ministry of finance, Minister of Agriculture
Ato Solomon Gebremariam – Director, vice miniter in various ministries
Ato Tesfaye Bushen – Vice minister of ministry of Agriculture and Governor of Arusi
Ato Teshome Gebremariam – Chairperson in the kinistry of Justice, vice minister of ministry of mines
Ato Olena Natnael – Vice minister of Finance and monitory fund
Ato Efrem Boru – Ambasador
Ato Molisa Rabu – Chiefe director in the ministry of Education

## Tigray:

Leul Ras Mengesha – Administrator of Tigray
Leul Ras Mengesha – Governor of Gibat and Mecha, Sidamo, Minister of labour and Communication
Ato Abebe Retta – Ambasador
Ato Belay Abay Kassa – Minister of Land and has been in charge of many other high ranking positions in the governement
Likemekuas Tadesse Negash – Chief director of ministry of Labour, Vice minister of ministry of Justice, Minster of Justice
Dejazmach Abbay Kassa – Governor of Chilalo
Dejazmach Kidane M hailu – Vice president of parliament
Ato Wendwosen Hailu – Ambasador
Nebured Gizaw Abera – Administrator Raija and Azebo, Aksum , member of the pariament
Lt. General Esayas Gebreselassie – Commandor of the armed forces, Governor of Sidamo
Ato Yohanes Kidanemariam - ?
Col. Simret Medhine Gebra – Chief of the Air force pilots, The first administretor of Ethiopian Airlines, Minister of labour, minister of city planning
Doctor Mengesha Gebre Hiwot – Vice minister of ministry of education
Ato Yohannes welde Gerima – Vice Mayor of Addis Abeba, vice minister of minitry of labour
Major Mesfin Yebegaeshet – Ambasador and Special Envoy
Dejazmach Gebre Hiwot Meshesha – Adminstrator of Ticho and also Shire
General Nega Haileselassie – Adminstrator
Ato Kidanewold haile – Ambasador
Doctor tesfaye Gebre Egzi – Minister of Information

## Gurage:

Dejazmach gebremariam Gari –Country Administrator
Dejazmach Kifle Ergettu – Minister of Interior
Lut. General Weldeselassie Berka – Comandor of special forces in the army, Comandor of the armed forces
General Welde Yohanes Shita – Second administreter of the Body Guard, Ambasador
General Teshome Ergetu – Comandor of the Armed Forces, Chief of the Eritrean Police
Ato Alfred Shafi – Director of Public administration, Vice minister of Interior and later a minister

Keng Azmach feleke Ergetu – (Has been in charge of Hizb Dehninet , Administrater, Minister
Lt. General Weldeselassie Bereka – Comander of spezial forces in the armed forces, Comander of the armed forces
Maj. General Yilma Shibeshi – Commander of the police force
Fitawrari Habtemariam weldekidan – Director under the ministry of Health, Administreter of Bahirdar and Gojjam
Ato Weldegebriel Ambaw – A judge in the Supreme Court
General Kifle Weldesenbet – Department Chief in the Ministry of Defence, In charge of education in the ministry of defence
General Gizaw Gebremikael – In charge of wealth and finance of the defence forces
Ato Seifu Dibaba – Administreter of Gojjam, Secretary trade and Finance, Oditor of minister of communication, Vice minister in the ministry of communication
Fitawrari Roga Ashame – Governer of the Lakes and Butagira
Maj. General Taye Balakir Sosum – Comander of Eritrean police force
Ato Haile Gebre Meskel – Yshewa administration wanna tekotatari
Azasz Hailu habte – Palace (Gibbi) Administreter
Ato Abebe ketema – Minister of health

## Afar, Harari and Sidama, Gemu Goffa, Somalia and Welaita:

Ato Minase Lemma – Minister of Money, Directer and Vice minister, Chief Oditor, Minster of mines, Chief of National bank of Ethiopia
Fitawrari Desta Fiseha Tona – Governer of Wolaita, Member of Parliament
Ato Bogale Waselu – Responsible of education in Sidamo
Ato Mulu Mojja – Judge in the Supreme court
Fitawrari Abayneh Fanno – Member of the parliament
Fitawrari Zewde Otoro – Member of the committee for jurisdication, Member of Parliament, Assistant Adminstreter of Sidamo
Ato Amanuel Habtegiworgis – Member of the Committee for Jurisdication and Judge of the Supreme Court
Fitawrari Mekonen Dori – Govrner of Geleb Hamar and Bakko, Assistance Administreter of Gemu Goffa
Bitweded Ali Mirah – Govrner of Adal and Isa, Chief Administeretr of Awassa
Ato Abdulahi Mume – Harer Custom Director, Assistance and Vice Minister in the ministry of Monetary Fund
Dejazmach Omar Samater – Administerter of Ogaden
Fitawrari Ahmed Ali Tase – Administrator of Harar
Fitawrari Ibrahim Hamid – Judge in the Supreme Court
Fitawrari Mume Arfo – Administeret of Yegaramulet
Fitawrari Sayed Weger – Administerter
Dejazmach Adem Abdu Lemer – Administreter of Wenbera

## Eritrea :

Bilaten Geta Lorenz Teezaz – Different post under various ministries, Advisor of the Crown and Minister of Foreign Affairs
Bilaten Geta Efrem Tewlde Medhin – Special envoy for king Haileselassie, Minister of agriculture, Member of the Parliament
Bitweded Asfha Welde Mikael – Special Envoy for Affairs concerning Eritrea , Minster of Health, Advisor of the Crown
Dejazmach Tedla Bahru – Special Envoy for Eritrean Parliament, Assistant administreter of Eritrea
Dejazmach Tesfayohanes Berhe – Special Envoy for the Eritrean Parliament,
Dejazmach Haregot Abbay – Mayor of Eritrea
Bilata Kifle Egzi Yihdego – Judge in the Supreme Court, Affe Negus in the Supreme Court
Bilata Dawit Ekube Egzi – Special envoy of the king, Assistant minister in the ministry of Foreign Affairs

Ato Seyoum Haregot – Assistant Prime minister, In the Prime ministers office Yeastedader Wanna Halafi
Ato Melese Mikael Andom – Special Envoy for the crown
Ato Tesfaye GebreEgzi – Ambasador, Assistance minister in the ministry of foreign Affairs and ministry fo Information
Doctor Solomon Abrha – Behager Astedader Wanna director, Vice minister
Dejazmach Gebre Yohanes Teklemariam – Ambasador, Minister in the ministry of Education
Ato Sereke Berhan GebreEgzi –Ambasador, Assistant minister in the ministry of Foreign Affairs,
Ato Araya Ekube Egzi – Ambasador – Chief commissioner of Tourism, Assistance minister in the Ministry of Foreign Affairs
General Yakob Gebre Leul – Commander of various divisions of the Armed forces
General Aman Andom – Commander of the armed forces and member of the parliament
General HaYile Baikedang – Commander of the first and second armed divisions
Maj. General Mebratu Fiseha – Assistant Chief of the Police force, Assistant minister maritiems, Assistant administrator of Gamu Goffa
Doctor Ambaye Gebremariam – Ambasador, Vice minister in the ministry of Justice
Ato Osman Muhammed – Ambasodor, Yehizb Habt Mikitil Minister, Assistant minister of Mayors
Ato Melakeselam Dimitros – Yeaksum Neburid, Beminister Dereja Yeabyote Kirstianat Wanna Asfetsami, Member of the parliament
Ato Hagos Tewlde Medhin – Assistant administrative minister in the ministry of Agriculture, Chief Judge, Mikitil Afe Negus
Ato Yohanes Tsige – Ambasador, Assistant minister in the ministry of Healt
Doctor bereketeab Habteselassie – Professor in Addis Abeba University , Yehager Mikitil Astedadari, Wannana Mikitil Akabe Hig, Mikitil Yehager wist Astedader Minister
General Asefa Gebre Egzi – Commander of Safty Flight operation, Assistant commander of the Air Force
Doctor Abrham Demoz – Assistance and Professor of Linguistics and history

## During The Time Of The Derg And Mengistu Hailemariam:

Col. Mengistu Hailemariam - President (Father Oromo, Mother Wolaita and Not as claimed Amara.)
Col. Debela Dinsa- Member of Office of the Police Force and Vice President
Ato Yesuf Ahmed – Vice President
Colonel Tekka Tullu – Member of the Police Force and Yedehninet Halafi
Colonel Tesfaye Weldeselassie – Member of the Politburou
Doctor Geremew Debele – Ambassador and Minister of Agriculture
Ato Tesfaye Dinka – Member of the Politburou, Minister of Agriculture, Minister of Money, Minister of Industry and Foreign Affairs, Prime Minister
General Tesfaye Gebrekidan – Member of the Politburou, Minister of Diffence and later on President
Capitan Mengistu Gemechu – Special Aid and Advisor for col. Mengistu Hailemariam
General Mesfin Gebrekal –Armed forces operational and political Chief
General Fiseha Desta – Member of the Politburou and Vice President
Doctor Berhane Gebrayi – Central Comitee member of the Ethiopian Workers Party, Ambasador, Assistant minister in the ministry of Education
General Yaditu Girumu – Chief of the Addis Abeba Police
Doctor Duri Muhammed – President of Addis Abeba University ,
Ato Simon Galore – Chief of Ethiopian Workers Party in Southern Ethiopia
Ato Tadese – General Maneger of the National Bank of Ethiopia , Minister of Foreign Trade and Ambasador